የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ
NATIONAL ELECTION BOARD OF ETHIOPIA

ቁጥር ፖ/1162/11/832

ቀን 2 5 2015

ለአፋር ህዝብ ፍትሐዊ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ

ሰመራ

ጉዳዩ፣ **የፓርቲውን ጠቅላላ ጉባዔ በድጋሚ እንዲደረግ ቦርዱ የሰጠውን ውሳኔ ስለማሳወቅ፤**

ሰኔ 17 ቀን 2014 ዓ.ም. በቁጥር አህፍደፓ/048/2014 በተጻፈ ደብዳቤ ፓርቲው ሰኔ 11 ቀን 2014 ዓ.ም. ያካሄደውን ጠቅላላ ጉባኤ በሚመለከት ሪፖርት ማቅረባችሁ ይታወቃል።

ስለሆነም ቦርዱ ታህሳስ 19 ቀን 2014 ዓ.ም. ባካሄደው ስብሰባ ፓርቲው ከሪፖርቱ ጋር አያይዞ ያቀረባቸውን ሰነዶች ከሕጉ፣ ከፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ እና የቦርዱ ታዛቢዎች ካቀረቡት ሪፖርት አንፃር መርምሯል።

**ጠቅላላ ጉባዔውን በተመለከተ**

በፓርቲው ጠቅላላ ጉባኤ የተካሄደው የፓርቲ ሊቀመንበር፤ ምክትል ሊቀመንበር እና የፓርቲው ዋና ጸሐፊ ምርጫ እጅ በማውጣት መደረጉ በአዋጅ አንቀጽ 74(3) መሠረት ሚስጥራዊ በሆነ መልኩ ያልተደረገ እና የሕጉን አስገዳጅ ድንጋጌ የተቃረነ በመሆኑ ፓርቲው ሕጉን መሠረት በማድረግ በድጋሚ ጠቅላላ ጉባኤ ሊካሄድ እንደሚገባ ቦርዱ ወስኗል፡፡

**የመተዳደሪያ ደንቡን በተመለከተ**

ሀ) በአዋጅ ቁጥር 1162/2011 አንቀጽ 74(1) (ፕ) መሰረት የፓርቲው የውስጥ አለመግባባቶች አፈታት ስርአት በመተዳደሪያ ደንቡ ውስጥ ያልተካተተ በመሆኑ በሕጉ መሠረት በማካተት እንዲቀርብ፤

ለድምጽዎ የሚያምኑን

አድራሻ - ቦሌ ክፍለሚንን
ሬስቶራንት ገባ ብሎ በስተቀኝ
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ

ስልክ
+251 115 153468

ፋክስ
+251 115 510025

ፌስቡክ
/national-electoal-board-of-ethiopia-nebe

ትዊተር
@NEBEthiopia

ኢሜይል
contact@nebe.org.et

ድረ - ገጽ
www.nebe.org.et

**ለ)** በተሻሻለው መተዳደሪያ ደንብ ምዕራፍ አምስት አንቀጽ 34 የፓርቲው የውስጥ አለመግባባቶች አፈታት ስርአትን በሚመለከት የተቀመጠው ድንጋጌ ግልጽ ያልሆነ እና ዝርዝር ጉዳዮችን ያላስቀመጠ በመሆኑ ማስተካከያ ተደርጎበት እንዲቀርብ ቦርዱ ወስኗል፡፡

በመሆኑም ፓርቲው በአዋጁ መሠረት በድጋሚ ጠቅላላ ጉባኤ እንዲያካሂድ እና ተሻሽሎ የቀረበው የፓርቲው መተዳዳሪያ ደንብም ከላይ በተራ ቁጥር "ሀ" እና "ለ" የተገለፁትን በሕጉ መሠረት በማካተት ሊሻሻል እና በጠቅላላ ጉባኤው ሊጸድቅ ይገባል ሲል ቦርዱ ወስኗል፡፡

**በዚሁ መሰረት፡-**

**1ኛ/** ፓርቲው ይህ ውሳኔ ከተገለጸበት ከታህሳስ 25/2015 ዓ.ም ጀምሮ በአራት ወራት ጊዜ ውስጥ ማለትም እስከ መጋቢት 25/2015 ዓ.ምድረስ ጠቅላላ ጉባኤ እንዲያካሂድ፤

**2ኛ/** የአመራር ምርጫን በሚመለከት ጉባኤው በሕጉ መሠረት መከናወን ያለባቸውን ሂደቶች የድምፅ አሰጣጥ፣ የድምፅ ቆጠራ እና ውጤት አገላለፅ በሕጉ መሠረት በሚስጥር እንዲከናወኑ እንዲያደርግ፤

**3ኛ/** ፓርቲው ከላይ በተራ ቁጥር **"ሀ" እና "ለ"** የተገለፁትን የመተዳደሪያ ደንብ ማሻሻያ የመተዳደሪያ ደንቡ አንቀፆች ላይ ማሻሻያ በማድረግ ጠቅላላ ጉባኤ ከመካሄዱ በፊት ማሻሻያ የተደረገባቸው የመተዳደሪያ ደንቡን አንቀፆች የተካተቱበት ረቂቅ መተዳደሪያ ደንብ ጉባኤው ከሚካሄድበት 5 የስራ ቀናት አስቀድሞ ለቦርዱ እንዲያቀርብ፤

**4ኛ/** ከላይ የተገለፁት ማስተካከያዎች የተደረገበት እና በቦርዱ በቅድሚያ የታየ የተሻሻለ የመተዳደሪያ ደንብ ለጠቅላላ ጉባኤው አቅርቦ በማስወሰን እንዲያቀርብ፣

**5ኛ/** ፓርቲው የጉባኤው ዝርዝር ሂደት እና ውሳኔ የሚገልጽ ቃለ ጉባኤ፣ በጉባኤው የፀደቀውን መተዳደሪያ ደንብ እና የጠቅላላ ጉባኤውን ሪፖርት ጉባኤው በተካሄደ በ15 ቀናት ውስጥ እንዲያቀርብ ቦርዱ የወሰነ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

ከአክብሮት ሰላምታ ጋር

ውብሸት አየለ ጌጤ
Woubshet Ayele Gete
የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ም/ሰብሳቢ
Deputy Chairperson National Electoral Board